**SmaRT Ethiopia**

CGIAR INITIATIVE ON Sustainable Animal Productivity



Photo ICARDA/Girma T. Kassie

# የገበያ መረጃ በበግና  ፍየል አርቢዎች የገበያ ተሳትፎ እና ገቢ ላይ ያመጣው ለውጥ

*በኢትዮጵያ ውስጥ ከተደረገ ሙከራ የተገኘ ማስረጃ*

## ቁልፍ መልዕክቶች

- በገጠሪቱ ኢትዮጵያ የሚኖሩ የበግ እና ፍየል አርቢ አርሶ አደሮች በግ እና ፍየል ለመሸጥም ሆነ ለመግዛት ሲወስኑ ግብዓት ሊሆናቸው የሚችል ወቅታዊ እና በቂ የሆነ የገበያ መረጃ በሚያረካ ደረጃ ባስ ሲልም በጭራሽ አያገኙም።
- ሰፊ ይዘት ያለው ወቅታዊ የገበያ መረጃ ማግኘት የበግ እና ፍየል አርቢዎች በተሻለ እና ዉጤታማ በሆነ መልኩ በገበያዎች እንዲሳተፉ ያስችላቸዋል።
- በማዕከላዊ የኢትዮጵያ ደጋማ አካባቢ 800 የበግ እና ፍየል አርቢ አርሶ አደሮችን ያካተተ ጥናት ተደርጎ ነበር። ለ 400 የበግ እና ፍየል አርቢዎች በሁለት ሳምንት አንድ ጊዜ የገበያ መረጃ የተላከላቸው ሲሆን ተመሳሳይ መረጃ ካልተሰጣቸው ሌላ 400 የበግ እና ፍየል አርቢ አርሶ አደሮች ጋር የንፅፅር ጥናት ተካሂዷል።
- መረጃውን ያገኙ አርሶ አደሮች በገበያው ሁናቴ ተስፋ በመቁረጥ ቶሎ እንስሳቱን ከእጅ የማውጣት ባህርያቸው የቀነሰ ሲሆን የገበያው ዋጋም ያልተመቻቸው ከሆነ በሌላ የገበያ ቀን ለመሸጥ የሚወስኑበት አግባብ ጨምሮ ታይቷል። እነዚህ አርሶ አደሮች ዘና ብለው እና ገበያ ላይ የተለመደው ወከባ ሳያስፈራቸው በግ እና ፍየሎቻቸዉን ይዘው ወደ ገበያ እንደሚሄዱም ገልጸዋል።
- መረጃው የተሰጣቸው አርሶ አደሮች መረጃው ካልተሰጣቸው ጋር ሲወዳደሩ በ20% ከፍ ያለ የገንዘብ ገቢ ከበግ እና ፍየሎቻቸው አግኝተዋል። እንደዚሁም በ32% ከፍ ያለ አጠቃላይ የጥሬ ገንዘብ ገቢ ያገኙ ሲሆን በተጨማሪ በንጽጽር በአመት ውስጥ በ85% ከፍ ያለ የበግ እና ፍየል ሽያጭ አከናውነዋል።
- የእንስሳት ገበያ መረጃን በጥራት እና በወቅቱ ለአርሶ አደሮች እንዲደርስ ማድረግ በገጠር ለሚኖረው ኢትዮጵያዊ ኑሮ መሻሻል ትልቅ ዋስትና ነው።

## መ ግ ቢ ያ

Photo ILRI/Apollo Habtam



በገጠሪቱ ኢትዮጵያ በሚኖረው ህዝብ ኑሮ ውስጥ በጎች እና ፍየሎች ከፍተኛ ሚና አላቸው። የቅርብ ጊዜ ጥናቶች እንደዘገቡት የቀንድ ከብቶች የምርት ውጤት እና አስተዋጽኦ እየቀነሰ ሲሆን በአንጻሩ የበግ እና ፍየል ድርሻ እየጨመረ ነው። ምንም እንኳን አስፈላጊነታቸውና ቁጥራቸው እየጨመረ ቢመጣም ለበግ እና ፍየል በተለይ እና በአጠቃላይ ለቀንድ ከብቶች ምርታማነት እና የግብይት ስርዓታቸውን ለማሻሻል የሚሰጠው ትኩረት አናሳ ነው።

ግብይትን በተለይ ስንመለከት እንስሳት አርቢዎች ዉስን ገበያዎች ዘንድ ብቻ ስለሚደርሱ እና ገበያዎችም መሰረታዊ ልማት የተነፈጋቸው ስለሆነ ከበግ እና ፍየል እርባታቸው ከቁም ከብት ዉጭ ለገበያ ምንም ነገር አያቀርቡም። የደላሎችና የነጋዴዎች ሸር እና ተንኮል፣ የመሠረተ ልማቶች አለመኖር እና ደረጃውን የጠበቀ የገበያ መረጃ እጥረት አርሶ አደሮች ከበግና ፍየሎቻቸው ሊያገኙ የሚገባቸውን ጥቅም እንዳያገኙ አድርጓቸዋል። ስለሆነም ለገበያ መረጃ ያላቸውን ተደራሽነት በማሻሻል፣ የግብይት ወጭዎችን በመቀነስ፣ የእንስሳት ግብይትን በማመቻቸት የድሃ አርሶ አደሮችን ሕይወት መለወጥ እና የእንስሳት እርባታው ዘርፍ ለኢኮኖሚው የሚያደርገውን አስተዋጽኦ ማሻሻል ይቻላል።

ILRI INTERNATIONAL LIVESTOCK RESEARCH INSTITUTE

ICARDA Science for resilient livelihoods in dry areas

በቅርቡ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያሳዩት በገበያ መረጃ አጥረት እና በሌሎች ምክንያቶች አነስተኛ ይዞታ ያላቸው አርሶ አደሮች ከእንስሳቶቻቸው የሚያገኙት ገቢ እጅግ ዉስን ነው:: እነዚህ አርሶ አደሮች ምርቶቻቸውን ለመሸጥም ሆነ የሚያስፈልጓቸውን ነገሮች ለመግዛት በመኖሪያ ቤታቸው አካባቢ ካሉ ገበያዎች አልፈው የሚሄዱት የግድ ሲሆንባቸው ብቻ ነው:: በወቅቱ እና በጥራት የሚቀርብ የገበያ መረጃ ግልጽ እና ስውር የሆኑ የግብይት ወጭዎችን ይቀንሳል:: ከዚህም የተነሳ አርሶ አደሮች ለምርቶቻቸው የተሻለ ዋጋ ሊያገኙ ይችላሉ::

በኢትዮጵያ ዉስጥ ምንም እንኳ የገበያ መረጃ ስርዓትን ለመዘርጋት ጥረቶች የተደረጉ ቢሆንም አርሶ አደሮች ከተደረጉት ጥረቶች ተጠቃሚ አልሆኑም:: በኢትዮጵያ ውስጥ ዋናውና የተደራጀው የእንስሳት እርባታ ዘርፍ የገበያ መረጃ ስርዓት በ2011 (እ.ኢ..አ) በመንግስት የተቋቋመዉ ብሔራዊ የእንስሳት ገበያ መረጃ ስርዓት ነው::

ይህ ስርዓት የሚጠቀመዉ በተቀንቀሳቃሽ ስልኮች አማካኝነት በማእከል ከሚገኝ የመረጃ ቋት በሚላኩ የጽሁፍ መልዕክቶች ሲሆን መጠኑ እና የዋጋው መረጃ በእንስሳቱ ዝርያ፣ በዕድሜያቸው፣ በጾታቸው እና በደረጃቸው በመለየት በአገሪቱ ላሉ አርባ ሰባት ገበያዎች ይልካል:: የመረጃዉ ይዘት በየጊዜው ይሻሻላል:: የዚህ ሥራ መኖር በተለያዩ የመንግስት እርከኖች የሚሠሩትን የተመሳሳይ ሥራ ድግግሞሽን ያስቀራል:: በተጨማሪም ጽሑፎችን፣ ምስሎችንና ድምጾችን ወደ ዲጂታል የመለወጥ እንዲሁም የእንስሳት ገበያ መረጃዉ ከመሠራጨቱ በፊት የሚደረገውን ትንተናና የማደራጀት ሂደትን አሻሽሏል:: ሆኖም ግን ስለ መረጃ ስርዓቱ ያለው ግንዛቤ አነስተኛ መሆን እና በቴክኖሎጂዎቹ ለመጠቀም ያሉት ችግሮች አገልግሎቱን በሰፊው ከመጠቀም የሚገድቡ ሆነው ተገኝተዋል::

የገበያ መረጃዎች ለምን እንደሚያስፈልጉ እና የገበያ መረጃ ስርዓቶች እንዴት መቋቋም እንዳለባቸው ለውሳኔ ሰጭዎች ለማሳወቅ ተጨባጭ ማስረጃዎች ያስፈልጋሉ:: ይሁን እንጂ እነዚህ ተጨባጭ ማስረጃዎች በኢትዮጵያ አይገኙም:: ይህ የሆነበት ምክንያት ደግሞ በኢትዮጵያ ዉስጥ በሥራ ላይ የዋለ እና ለአርሶ አደሮች ተደራሽ የሆነ የእንስሳት ገበያ መረጃ ስርዓት ስለሌለ ነው:: ይህንን ክፍተት ለመሙላት ዓለም አቀፍ የቆላ አካባቢ የምርምር ማዕከል ከሌሎች ዓለም አቀፋዊና ብሔራዊ አጋሮች ጋር በመተባበር ዘመናዊ የግብይት ስርዓት ለዘመናዊ የበግ እና ፍየል የእሴት ሰንሰለት ልማት የተሰኘ ጥናት አካሂዷል:: ይህ ጽሑፍ በዚህ ጥናት አማካኝነት የተገኘዉን መረጃ እና ልምድ ባጭሩ ያቀርባል::

## የተጠናው አዲስ ቴክኖሎጂ

በቅድሚያ የበግ እና ፍየል የገበያ መረጃ የሚሰበሰብበት፣ የሚተነተንበት እና ዉጤቱ የሚገለጽበት አሰራር ተዘረጋ:: በመቀጠልም ገበያ የሚቀርቡ በጎች እና ፍየሎች ባህርያት እና ገዢዎች ለባህርያቱ ያላቸው አመለካከት፣ የበግ እና ፍየል ዋጋ ግምቶች፣ በገበያ የሚፈለገው የበግ እና ፍየል መጠን፣ የሚቀርበዉ የበግ እና ፍየል መጠን፣ በገበያ ዉስጥ ያሉ አገልግሎቶች እና ገበያዉን ሊያዉኩ የሚችሉ ማህበራዊ እና የተፈጥሮ ክስተቶች ላይ የመረጃ ስብሰባ ተጀመረ:: መረጃዎቹ የተሰበሰቡት በየሳምንቱ በእያንዳንዱ ገበያ ዉስጥ ሲሆን መረጃዎች የተሰበሰቡት ወጥ የሆኑ መጠይቆችን በመጠቀም ነው:: በዚህ መልኩ የሁለት ሳምንት መረጃ ተደራጅቶ፣ ተጣርቶ፣ ተተንትኖና ለአጠቃቀም እንዲመች ሆኖ ለአርሶ አደሮች ቀርቧል:: መረጃው ለተመረጡ አርሶ አደሮች የተላከው በተቀንቀሳቃሽ ስልክ አማካኝነት ነው::

## የጥናቱ ዓላማ እና ስልት

የገበያ መረጃ መዋቅሩ በ2009/10 ዓ/ም በሰሜን ሸዋ ዞን መንዝና ጊሼ አካባቢ ዉስጥ ባሉ እና በእጣ በተመረጡ ስምንት የበግ እና ፍየል ገበያዎች የተሞከረ ሲሆን ሌሎች በዛው አካባቢ ያሉ ስምንት የበግ እና ፍየል ገበያዎች ደግሞ ለማነጻጸሪያነት ተካተዋል:: ጥናቱ የተጀመረው ከአስራ ስድስቱም ገበያ ከእያንዳንዳቸው ሃምሳ የበግ እና ፍየል አርቢዎች በእጣ በመምረጥ ነበር:: በመቀጠልም የመነሻ ቅኝት ተደርጎ አርሶ አደሮቹ ያሉበትን ሁኔታ የሚያሳይ ሰፋ ያለ መረጃ ተሰብስቧል:: ሙከራው ለ12 ወራት ተካሂዷል:: ሙከራው ከተጠናቀቀ በኋላ አርሶ አደሮቹ የደረሱበትን ደረጃ ለመረዳት የመጨረሻ ዳሰሳ ጥናት 2012/13 ዓ/ም ተካሂዷል::

ሙከራው በስምንቱ የሙከራው ተሳታፊ የበግ እና ፍየል ገበያዎች ዙሪያ ላሉ 400 አርሶ አደሮች ተንቀሳቃሽ ስልኮች ማደልን ያካተተ ነበር:: ይህ ሊሆን የቻለበት ምክንያት አስቀድሞ የተካሄደው የዳሰሳ ጥናት ከተሳታፊ ቤተሰቦች ውስጥ ተንቀሳቃሽ ስልክ የነበራቸው ቤተሰቦች 4% ብቻ መሆናቸውን በማሳየቱ ነው:: ተንቀሳቃሽ ስልኮቹ ከታደሉ በኋላ የመረጃ መሰብሰቡና ለአርሶ አደሮች በየሁለት ሳምንቱ የማሰራጨት ሥራ ተጀመረ:: ሙከራው ከተጠናቀቀ በኋላ ለአምሳ ሳምንታት መረጃ የተሰበሰበ ሲሆን መረጃውን እንዲያገኙ ለተመረጡት አርሶ አደሮች በሃያ አምስት ዙር እንዲደርሳቸው ተደርጓል::

*ምስል 1: መረጃውን ያገኙና (ናሙና) መረጃውን ያላገኙ (ንጽጽር) ገበያዎች*

| መረጃውን ያገኙ | መረጃውን ያላገኙ |
|---|---|
| ባሽ | ደል |
| ግራር አምባ | ገይ |
| ወጀድ | አሸን |
| ቆሎ ማርገፊያ | መሃል ሜዳ |
| ሞላሌ | መለያ |
| ይገም | ራቤል |
| ዘመሮ | ሸሾ |
| ዘረት | ወገሬ |



Photo ICARDA/Girma T. Kassi

*ለተሳታፊ አርሶ አደሮች ተንቀሳቃሽ ስልክ ሲታደል*

## የተገኙ ዉጤቶችና ማስረጃዎች

መረጃ ከሚላክላቸው አርሶ አደሮች ጋር የሚደረጉ ተከታታይ የቡድን ውይይቶች እና ከመስክ አስተባባሪዎች የሚገኙ መረጃዎች በቤተሰብ ደረጃ የተገኙ ለውጦችን ለመከታተል ጥቅም ላይ ዉለዋል። ክትትሉ አርሶ አደሮቹ እራሳቸው ለይተው ያወቋቸውን የባሕርይ ለውጦችን እና በጊዜ ሒደት የመጡ ለውጦችን ለመመዝገብ ጠቅሟል። መረጃው የተሰጣቸው አርሶ አደሮች ለይተው ያስቀመጧቸው ለውጦች የሚከተሉት ናቸው፦

- የበግ እና ፍየሎቻቸውን ዋጋ ለመደራደር በራስ የመተማመን ስሜታቸው ጨምሯል።
- አርሶ አደሮች የእንስሳት ገበያን በተመለከቱ ጉዳዮች እና በሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች ላይ ከበፊቱ ለበለጠ ጊዜና የበለጠ በዳበረ ሁኔታ እርስ በርስ መወያየት ችለዋል።
- ገበያው ስላለበት ሁኔታ በደንብ ማወቃቸው በግ እና ፍየል ወደ ገበያ ይዘው ለመሄድ የመበረታታት ስሜት ፈጥሮባቸዋል። እነሱ ራሳቸው እንደሚገልጹት አሁን እንደ ቀድሞ ገበያ ውስጥ እንዋከባለን ብለው አይሰጉም።
- ገበሬዎቹ የመሸጥ ወይንም የመግዛት ውሳኔያቸውን መቀየር አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኙ ይህንኑ ማድረግ እንደቻሉ ለማወቅ ተችሏል። በአካባቢው የሚኖሩ አርሶ አደሮች የሚሸጡበትን ጊዜ ለማራዘምም ሆነ ማራዘሙን እንደ አንድ አማራጭ ለማየት የሚያስችል የመረጃ ድጋፍ አግኝተዋል።

ከላይ እንደተገለጸው ከስምንት መቶ በግ እና ፍየል አርቢዎች በሁለት ዙር መረጃ ተሰብስቦ የገበያ መረጃ አቅርቦቱ መረጃዉ ለተላከላቸው አራት መቶ በግ እና ፍየል አርቢዎች ያለዉን ፋይዳ ለመለካት ተሞክሯል። የፋይዳዉ ጥናት የመረጃ አቅርቦቱ ከበግ እና ፍየል የሚገኘውን ገቢ፣ አመታዊ አጠቃላይ የጥሬ ገንዘብ ገቢ እና በቤተሰብ ደረጃ የበግ እና ፍየል ሽያጭ ላይ ያስከተለዉን ለውጥ ገምግሟል።

መረጃን ያገኙ አርሶ አደሮች ካላገኙት ጋር ሲነጻጸር ከበግ እና ፍየል ሽያጭ በአመት ውስጥ በ20.1% የበለጠ ገቢ አግኝተዋል። በመንዝ ግሼ አካባቢ የአርሶ አደሮች ኑሮ በበግ እና ፍየል ላይ በከፍተኛ ደረጃ ጥገኛ የሆነ ነው። በዓመት ውስጥ ከበግ እና ፍየል የሚገኝ ገቢ በ20% መጨመር ብዙ ላይመስል ይችላል። ሆኖም ግን በአገሪቱ ውስጥ ካሉ ለኑሮ ከማይመቹ አካባቢዎች አንዱ በሆነው እና ገቢያቸውን ለማብቃቃት ለሚዋትቱ የመንዝ ግሼ አካባቢ አርሶ አደሮች በእርግጥም ትልቅ ነገር ነው። በጎች እና ፍየሎች ጥናቱ በተደረገበት ቦታ ካላቸው ጠቀሜታ አኳያ በገበያ መረጃ ላይ ጊዜን መመደብ እና ገንዘብ ማውጣት የገበሬውን ኑሮ ትርጉም ባለው ደረጃ ይቀይረዋል።

የገበያ መረጃ ያገኙ ቤተሰቦች ካላገኙት ቤተሰቦች ጋር ሲነፃፀር በ32% ከፍ ያለ አጠቃላይ አመታዊ የጥሬ ገንዘብ ገቢ አግኝተዋል። በበግ እና ፍየል የተገኘው ገቢ ደግሞ የመባዛት ባህርይ አለው። ይህ የሚሆነው የገበያ መረጃ ያገኙ አርሶ አደሮች ከበግ እና ፍየል እርባታ ውጭ በሆኑ በሌሎች ስራዎችም ቢሆን የበለጠ ገቢ ማግኘት ስለቻሉ ነው። በገበያ ውስጥ መሳተፋቸውም ለማምረት እና ለግብይት አስፈላጊ ለሆኑ ቁልፍ ግብዐቶችና አገልግሎቶች ያላቸው ቅርበት እንዲጨምር አድርጓል። ስለሆነም የገበያ መረጃ ማግኘታቸው የበግ እና ፍየል አርቢዎች በጥሬ ገንዘብ የሚያገኙት ገቢ እንዲጨምር አድርጓል ማለት ይቻላል።

የገበያን ተሳትፎ ለመገመት ከምንጠቀምባቸው መንገዶች አንዱ እና በጣም የተለመደው የተጣራ ሽያጭ ነው። የተጣራ ሽያጭ የሚባለው በአንድ ዓመት ውስጥ በበግ እና ፍየል አጠቃላይ ሽያጭ እና ግዥ መካከል ያለው ልዩነት ነው። የትንተናው ውጤት እንደሚያሳየው የገበያ መረጃ ያገኙ የገበሬ ቤተሰቦች መረጃውን ካላገኙት ጋር ሲነፃር በ85% የበለጠ በግ እና ፍየል በዓመት ውስጥ ሸጠዋል። መረጃውን ያገኙ የገበሬ ቤተሰቦች እንደገለጹት ከሆነ እንስሶቻቸውን ወደ ገበያ ለመውሰድ በራስ መተማመን እንደሚሰማቸው እና በዚህም ምክንያት መረጃውን ካላገኙት ቤተሰቦች ይበልጥ ብዙ ጊዜ እንስሶቻቸውን መሸጥ መቻላቸውን ገልጸዋል።



Photo ICARDA/Girma T. Kassi

*የበግ እና ፍየል ገበያ በያቤሎ ደቡብ ኢትዮጵያ*

## የስኬት ምክንያቶችና ለፈጠራዉ አስተዋጽዖ ያደረጉ ጉዳዮች

የግብርና ዘርፍ ዕድገት በትክክል የሀገሪቱ አጀንዳ ከሆነ የእንስሳት ግብይት ልማት ችላ መባል የሌለበት ጉዳይ ነው:: የገበያ ልማት በዋነኝነት የሚያጠነጥነው የመረጃን አለመመጣጠን እና የግብይት ወጭዎችን በመቀነስ ዙሪያ ነው:: ጥናቱ በተካሄደበት አካባቢ ያሉ አርሶ አደሮች የገበያ ስጋቶችን ለመቀነስ ወይንም የእንስሶቻቸውን ዋጋ ለመጨመር የሚያስችል ድጋፍ ለማግኘት በጣም ይጓጓሉ::

ከአርሶ አደሮች ጋር የተደረጉ ምክክሮች ስኬታማ የሆነ የገበያ መረጃ ስርዓት ዘርግቶ ለመተግበር የሚያስችሉ ብዙ ሁኔታዎችን ለመለየት አስችሏል:: የገበያ መረጃ ስርዓት ግንባታ መጀመር ያለበት አርሶ አደሮችን እና ሌሎች ከገበያው ብዙም ጥቅም የማያገኙ ተሳታፊዎችን በገበያ ዋጋ አወሳሰን እና የገበያ መረጃ ሚና ላይ ያላቸውን ግንዛቤ ማዳበር ነው::  ግንዛቤው ያላቸው አርሶ አደሮች በኢትዮጵያ የእንስሳት ገበያ ላይ በጣም ጠንካራ የሆኑ ተዋንያንን፣ ማለትም ነጋዴዎችንና ደላሎችን በተለየ መልኩ መቅረብ እና ማስተናገድ እንዳለባቸው ይረዳሉ:: ይህን የሚያደርጉት የመረጃ ያለመመጣጠንን ምንነትና አንድምታውን ስለሚረዱ ነው::

ሁለተኛው ከግምት ሊገባ የሚባው ጉዳይ የእንስሳት ግብይት መረጃ ከሚኖረው አስተዋጾ አኳያ ያለው ትርጉም ነው:: ቀደም ብለው የተቋቋሙ የመረጃ ሥርዓቶች ቁልፍ ለሆኑት ለፍላጎትና ለአቅርቦት ተገቢውን ትኩረት ሳይሰጡ በዋጋ ላይ ብቻ ያተኮሩ ነበሩ:: ሆኖም በገበያ ውስጥ ፍላጎት እና አቅርቦት ወሳኝ መሆናቸውን በመረዳት እና በየወቅቱ ፍላጎትና  አቅርቦትን ምን እንደሚለዋዉጣቸው ከግምት ባስገባ መልኩ መረጃውን ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው:: በገበያ ውስጥ ስላሉ በግ እና ፍየሎች ልዩ ልዩ ባህርያት እና በፍላጎትና በአቅርቦት ዙሪያ ሊያጋጥሙ ስለሚችሉ ያልታሰቡ ክስተቶች መረጃ በማግኘታቸው የአርሶ አደሮች በራስ መተማመን የጨመረ ሲሆን የተሻለ ዋጋም እንዲከፈላቸው መደራደር ችለዋል::

ሌላው በስራዉ ላይ የተስተዋለው ቁልፍ ጉዳይ የገበያ መረጃን በተቻለ መጠን በፍጥነት እና አግባብ በሆነ ድግግሞሽ መስጠት አርሶ አደሮች በዕውቀት ላይ የተመሰረቱ ውሳኔዎችን እንዲወስኑ ያስችላቸዋል:: መረጃዎቹ ለአርሶ አደሮች በየሁለት ሳምንት በመላካቸው የመረጃው ጥልቀት ከመጨመሩም በላይ አርሶ አደሮች በመረጃው ላይ ተመስርተው ውሳኔ ወስነው ስለመሆናቸው የመተማመኑ ደረጃ ይጨምራል:: ይህም ሆኖ አርሶ አደሮች በየሳምንቱ አዳዲስ መረጃዎች እንዲሰጣቸው ያለማቋረጥ ይጠይቁ ነበር:: እዚህ ላይ መስተዋል ያለበት ጉዳይ ሰዎች አንዴ መረጃ ማግኘት ሲጀምሩ ለመረጃ ያላቸው ፍላጎት እንደሚጨምር ነው::

የገበያ መረጃ አቅርቦት አርሶ አደሮች የሚጠቀሙባቸውን ወይም የሚያውቋቸውን በርከት ያሉ ገበያዎች እና የተለያዩ የቀንድ ከብቶችን የሚሸፍን ከሆነ የበለጠ ጠቃሚ ይሆናል:: አርሶ አደሮች በራሳቸው ገበያ ላይ ደስ የሚያሰኝ ሁኔታ ሲፈጠር እና ሲመቻቸው በሌሎች ገበያዎቸ ውስጥ ምን እየሆነ እንደሆነ የበለጠ ማወቅ ይፈልጋሉ:: በገበያዎች መካከል ጠንካራ ትስስር አለመኖር በገበያዎች መካከል ያለዉን የዋጋ ልዩነት ተረድተዉ ያለአግባብ ለሚጠቀሙ ነጋዴዎች እና በርካሽ ገዝተዉ በዉድ ለሚሸጡ ሰዎች በር እንደሚከፍት ያውቃሉ:: በተመሳሳይ ሁኔታ በመረጃ ስርዓቱ ውስጥ የብዙ የእንስሳት ዝርያን መረጃ ማካተት አርሶ አደሮችን የበለጠ ይረዳቸዋል::

## የተገኘው ትምህርትና ለማስፋፋት መታሰብ ያለባቸው ጉዳዮች

በጥንቃቄ የተነደፈ የእንስሳት ገበያ መረጃ ሥርዓት በግብይት ሒደት አርሶ አደሮች ያሉባቸውን ስጋቶችን ከመቀነሱም ባሻገር የመደራደር አቅማቸውን ይጨምራል:: የእንስሳት እርባታ ባለዉ እምቅ አቅም እና ከዘርፉ በሚገኝ ጥቅም መካከል ያለውን ክፍተት ለመሸፈን በቂ  እና ወቅታዊ የገበያ መረጃ አስፈላጊ ነው:: በሙከራ ደረጃ በጥናቱ ቦታዎች የተሰጠው የገበያ መረጃ ለገበሬዎቹ በጣም ጠቃሚ እንደነበረ ግልጽ ነው:: እዚህ ተጨባጭ ግኝት ላይ በመመርኮዝ ሊባል የሚችለው ነጥብ ተገቢ ተቋማዊ ድጋፍ ካገኘ እና በትክክለኛ የአሰራር ሂደቶች ከታገዘ የገበያ መረጃ አቅርቦት በአገር አቀፍ ደርጃ ሊስፋፋና ትልቅ ሚና ሊጫወት እንደሚችል ግልጽ ነው::

የገበያን መረጃን ስርዓት ለማስፋፋት የሚረዱ አምስት ጉዳዮች የተለዩ ሲሆን እንደሚከተለው ቀርበዋል፦

1. በኢትዮጵያ **የተንቀሳቃሽ ስልክ እና የኢንተርኔት ተጠቃሚነት እየተስፋፋ ነው**:: ስለሆነም ዋጋቸው ውድ ያልሆኑ እና ለመጠቀም ቀላል የሆኑ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም የእንስሳት ግብይት መረጃን በስፋት ማሰራጨት ይቻላል::

2. የቴሌኮሙነኬሽን አገልግሎት ከመንግስት እጅ በመጠኑም ቢሆን እየወጣ መምጣቱ መልካም ጅማሮ ነው:: ሆኖም **የግል ዘርፉ ከዚህ በበለጠ ተሳታፊ እንዲሆን እና የዘርፉን ተወዳዳሪነት ኢንዲጨምር** ሁኔታዎች ሊመቻቹ ይገባል::

3. **ብሔራዊ የእንስሳት ገበያ መረጃ ስርዓት ሁሉን አቀፍ የሆነ የእንስሳት ገበያ መረጃ ስርኣትን ለመገንባት መነሻ መሠረት ሆኖ ሊያገለግል ይችላል።** ይህ ስርዓት በአርሶ አደሮች ፍላጎት እና ችሎታ ላይ ካተኮረ እና በገበያዎችና እና ገበያተኞች መካከል ያሉ ልዩነቶችን ከግምት የሚያስገባ ከሆነ በመረጃ ስርዓቱ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ የእንስሳት አርቢ ቤተሰቦችን መጥቀም ይቻላል::

4. አሁን እየተተገበረ ያለው **ብሔራዊ የግብርና ትራንስፎርሜሽን ፕሮግራም** የእንስሳት ገበያን የመረጃ ስርዓት ለማሳደግ ተገቢውን ጥረት ማድረግ እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ ለማሳየት ጥሩ አጋጣሚ ነው::

5. ልክ እንደማንኛውም አዲስ ተክኖሎጂ በግና ፍየል አርቢዎችን ስለ እንስሳት ገበያ መረጃ ሥርዓት ምንነት እና ፋይዳ በቅድሚያ ማስረዳት እና ግንዛቤን ማዳበር ያስፈልጋል::  **ግንዛቤን ማሳደግ እና ስለ መረጃ ሥርዓቱ በደንብ ማስተዋወቅ** የእንስሳት ገበያ መረጃ በአርሶ አደሮች የገበያ ብቃት ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ እንዲኖረው ያደርጋል::



Photo ILRI/Zerihun Sewunet

*ሳር በቦረና፣ ኢትዮጵያ የሚኖር አርብቶ አደር ነው:: ወቅቱን የጠበቀ እና ትክክለኛ የገበያ መረጃ ማግኘት እርሱን እና እሱን የመሰሉ ብዙ የበግ እና የፍየል አርቢዎችን ከከብቶቻቸው የበለጠ ገቢ እንዲያገኙ ያግዛቸዋል::*



Photo Mamusha Lemma, ILRI

*በወሎ፣ ኢትዮጵያ የሚኖሩ ገበሬ ከበጎቻቸው ጋር። ወቅቱን የጠበቀ እና ትክክለኛ የገበያ መረጃ ማግኘት እሳቸው እና እሳቸውን የመሰሉ ብዙ የበግ እና የፍየል አርቢዎች ከከብቶቻቸው የበለጠ ገቢ እንዲያገኙ ያግዛቸዋል።*

## ምስጋና

ይህ ምርምር፣ ዓለምአቀፍ የግብርና ምርምር አማካሪ ቡድን (CGIAR)፣ በእርባታ እንስሳት ላይ በሚያካሂደው የምርምር መርሃ-ግብር ውስጥ ሲደረግ ቆይቶ፣ በCGIAR ዘላቂ የእንስሳት ምርታማነት ኢኒሼቲቭ ውስጥም ቀጥሏል። የCGIAR ምርምር የገንዘብ ድጋፍ የሚያገኘው ከCGIAR Trust Fund አስተዋፅዖዎች ነው። CGIAR የምግብ ደህንነቱ የተረጋገጠበት መጪ ዘመን እንዲፈጠር የሚሠራ ሉላዊ የምርምር ሕብረት ሲሆን፣ በአየር ሁኔታ ቀውስ ውስጥ የምግብን፣ የመሬትን፣ እና የውሃን ሥርዓቶች ለማሻሻል በቁርጠኛነት ይተጋል። በተጨማሪም፣ እነዚህ የምርምር ወረቀቶች ወደአማርኛ እንዲተረጎሙ እና የገፅ ንድፋቸው እንዲሠራ፣ የCGIAR የአየር ሁኔታ ምርምርን ተፅዕኖ ማቀለጠፍ ለአፍሪካ (AICCRA) ለተሰኘው ፕሮጄክት የገንዘብ ድጋፍ ላደረገው የዎርልድ ባንክ አካል ለሆነው ዓለም-አቀፍ ልማት ማኅበርም (IDA) ምስጋና እናቀርባለን።

## አጋሮች

ስማርት ኢትዮጵያ ፕሮጀክት ከዓለም አቀፍ የእንስሳት ምርምር ተቋም (ILRI) እንዲሁም ከኢትዮጵያ ግብርና ምርምር እንስቲትዩት (NARS) ጋር በመተባበር በዓለም አቀፍ የቆላ አካባቢ ምርምር ማዕከል (ICARDA) የሚመራ ነው።

### ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት

ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ዶ/ር ግርማ ተስፋሁን ብለው በኢሜይል አድራሻችን g.tesfahun@cgiar.org ይጻፉልን።

*ይህን ህትመት ለመጠቀም ፍቃድ የሚሰጠው the Creative Commons Attribution 40 በተባለ ዓለም አቀፍ ፈቃድ ሰጭ በኩል ነው። ኦክቶበር 2021*